በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አፈፃፀም ላይ ለሚቀርቡ
አቤቱታዎች ማጣሪያና የውሳኔ አሰጣጥ
ትግበራ ማኑዋል

ጥቅምት/2005 ዓ.ም.

<u>ባህር ዳር</u>፣

መግቢያ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት፣ ለተገልጋዮች የሚሰጠውን የአገልግሎት ደረጃ ከፍ ለማድረግና ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግስት ገንዘብ የሚፈስበትን የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠርና ለመምራት የሚያስችለው አሰራር ላይ ለውጥ ለማምጣት የተሻሻሉና አዳዲስ የግዥና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎችንና ማኑዋሎችን አዘጋጅቷል። በመሆኑም በወጡት የህግ ማእቀፎች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እየሰጠ ያለ ከመሆኑም በተጨማሪ የእቃ፣የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥ አቀራቢዎች ወይም ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች የመነጩ ቅሬታዎችን በመቀበል የማማከርና ውሳኔ የመስጠት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

በዚህ መሰረት ከተጫራቾች፣ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ከስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ወይም ከግለሰብ ጠቋሚዎች ላይ የሚቀርቡ በግዢ አፈጻጸም ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች በኩል ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ መስጠት፣ እንዲሁም በመንግስት ንብረት ሽያጭ ጨረታ ላይ ከንብረት ገዢ ግለሰቦች በሻጭ መንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ወይም ንብረት ሻጭ መስሪያ ቤቶች በንብረት ገዢ ግለሰብ ላይ አቤቱታ ሲያቀርቡ ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አንድ መሰረታዊ የሆነ ተግባርና ሀላፊነቱ ነው።

ስለሆነም በዚህ የቅሬታ/የአቤቱታ ማጣሪያ ውሳኔ አሰጣጥ ማንዋል ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሉ የቅሬታ ማስተናግድ ተግባራት ቅደም ተከተል ምን እንደሚመስል፣ በሂደቱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ምን እንደሆኑና በመጨረሻ የሚገኘው ውጤት ምን እንደሆነ የሚያመልክት አሰራር እንደሚከተለው ቀርቧል።

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አፈጻጸም አቤቱታ ማጣሪያና ውሳኔ አሰጣጥ ተግባር አጠቃላይ መግለጫ

በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አፈጻጸም ሂደት ላይ በደል ደርሶብኛል የሚሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች ወይም ንብረት ገዥ ግለሰቦች ጉዳዩ እንዲታይላቸው አቤቱታ ሲያቀርቡ፣ በሌላ በኩል የመንግስት መ/ቤቶች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች ወይም ንብረት ገዢዎች በገቡት የግዥ ውል መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም ወይም ውል ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም፣ ወዘተ በሚል የጥፋተኝነት ሪፖርት ሲያቀርቡ፣ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአቅራቢዎች ክስ ቀርቦለት ከሙያ አኳያ እንዲጣራለት በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብ፣ እንዲሁም ስለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አፈጻጸም ጉድለት ከማናቸውም አካል ጥቆማ ሲቀርብለት አስፈላጊ የሆኑ መግለጫዎችና ማስረጃዎችን ከየሚመለከታቸው አካላት በማሰባሰብና የሚሰራባቸውን የህግ መዕቀፎች መሰረት በማድረግ አጣርቶ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን አሰራር በመከተል ተግባራዊ ያደርጋል።

1. **ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ወይም ንብረት ገዢ ግለሰብ ወይም ጠቅሚ ወይም የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ያቀረበው አቤቱታ ሲሆን፣**

ሀ/ በመጀመሪያ ጉዳዩ ከተፈጸሚነት ወሰንና ከጊዜ ከአፈጻጸም አኳያ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት የሚታይ መሆኑና አለመሆኑ በሚከተሉት መንገዶች ይጣራና ለእጩ ተወዳዳሪው ወይም ለተጫራቹ በዕሁፍ ምላሽ ይሰጠዋል፣

- እጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ ንብረት ገዢው ግለሰብ በመጀመሪያ ጨረታውን ላወጣው ባለበጀት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ማቅረቡንና አለማቅረቡ ይጣራል። አቤቱታውን ያላቀረበ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 57 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በመጀመሪያ ለመ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት አቤቱታ የሚቀርበው በአዋጁ አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ 1 ከነኪ 3 መሰረት እና በግዥ መመሪያው አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 መስሪያ ቤ/ቱ አቤቱታው በቀረበለት ለግዥ በ 4፣ ለንብረት ሽያጭ በ 5 የስራ ቀን ውስጥ ምላሽ ካልሰጠው ወይም የሰጠው ምላሽ ያላረካው መሆኑን ፣

- እጩ ተወዳዳሪው፣ተጫራቹ ወይም ንብረት ገዢው ግለሰብ ለመስሪያ ቤቱ አቤቱታ አቅርቦ ምላሽ ከተሰጠው ወይም በግዥና ንብረት አስተዳድር ህጉ መሰረት ምላሹን መስጠት ከሚገባው ከመጨረሻው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 የስራ ቀን ካለፈ በኋላ አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ልማት መ/ቤቶች ያቀረበ ከሆነ ጉዳዩ የማይታይ መሆኑን፣

ለ/ ከላይ በፊደል ሀ ላይ በተጠቀሰው አግባብ አቤቱታው የሚጣራ መሆኑ ሲረጋገጥ አቤቱታውን ለማጣራት የሚያስፈልጉ ከተጠቀሰው ግዢና ንብረት ማስወገድ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያላቸውን የሚከተሉትን ሰነዶች መስሪያ ቤቱ እንዲልክ የሚጠይቅ ማስታወቂያ በጽሁፍ በደረሰው በ3 የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡ የሚጠየቁት የግዢ ሰነዶች እንደ ግዢው ዘዴና ሁኔታ ሊለያዩ ይችላሉ፣

- ✓ ለግዥ ተጫራቾች የተሸጠ/የተሰጠ የጨረታ ሰነድ ወይም ለንብረት ሽያጭ የቀረበ የጨረታ ዝርዝር፣
- ✓ ተጫራቾች ያቀረቡት የመወዳደሪያ ሰነዶች፣
- ✓ የግዢ ወይም የንብረት ሽያጭ ጨረታ የግዥ ኦፊሰሮችን / የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴዎችን/ የጨረታ አከፋፈት፣ የግምገማ ሂደት፣ የውሳኔ አስተያየትና የማጽደቅ ኃላፊነት በተሰጠው ኃላፊ የተሰጠውን ውሳኔ የሚያሳዩ ቃለ ጉባኤዎች፣
- ✓ ለጨረታ አሸናፊና ተሸናፊዎች የጨረታ ውጤት የተገለጸበት ማስታወቂያ፣
- ✓ አሸናፊው ተጫራች ውሉን ቀርቦ እንዲፈርም የተገለጸበት ደብዳቤ፣
- ✓ ባለበጀት መስሪያ ቤቱና አቅራቢው የተፈራረሙት ውል፣
- ✓ ለተጫራቹ የተሰጠ የግዢ ትዕዛዝ (Purchase Order)፣
- ✓ ለንብረት ገዢው የተሰጠ የንብረት ማንሳት ትዕዛዝ፣
- ✓ ባለበጀት መስሪያ ቤቱ ከዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ከተጫራቹ ወይም ከንብረት ገዢው አቤቱታ ቀርቦለት ከሆነ የቀረበውን አቤቱታና የተሰጠውን የጽሁፍ ምላሽ፣
- ✓ ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ ወይም ንብረት ገዢው እና መስሪያ ቤቱ ግዢውን በተመለከተ በየጊዜው የተለዋወጡት ደብዳቤና መረጃዎች፣
- ✓ ስለተጠቀሰው አቤቱታ የጽሑፍ ማብራሪያና መግለጫ፣

ሐ/ አንድ አጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ምክንያቶች አቤቱታ ማቅረብ አይችልም፣

- ▪ በአዋጁ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ በተወሰነው የግዢ ወይም የሽያጭ ዘዴ ምርጫ፣
- ▪ በመንግስት ግዥ አዋጅ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለአገር ውስጥ ምርቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ስራዎች ወይም ለምክር አገልግሎቶች በተደረገ ልዩ አስየያየት፣
- ▪ በአዋጁ በተጠቀሰው መሰረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሳኔ፣
- ▪ በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው የሽያጭ መነሻ ዋጋ ላይ፣

2. **የመንግስት መ/ቤት በተጫራች ወይም በአቅራቢ ወይም በንብረት ግዢ ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ሲያቀርብ፣**

- ተጫራቹ ወይም አቅራቢው ወይም ንብረት ገዢው አቤቱታውን ለማጣራት የሚያስፈልጉ ከተጠቀሰው ግዢ/ሽያጭ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የሚከተሉትን ሰነዶች በ5 የሥራ ቀን ውስጥ እንዲልክ ደብዳቤ ይፃፍለታል፣ የሚጠየቁት የግዢ ሰነዶች እንደ ግዢው ዘዴና ሁኔታ ሊለያዩ ቢችሉም በሚከተሉት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፣

  - ✓ ከመስሪያ ቤቱ የተሸጠለትን ወይም የተሰጠውን የጨረታ ሰነድ፣
  - ✓ ለመስሪያ ቤቱ ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሰነድ፣
  - ✓ ለጨረታ አሸናፊና ተሸናፊዎች የጨረታ ውጤት የተገለጸበት ማስታወቂያ፣
  - ✓ አሸናፊው በመሆኑ ውሉን ቀርቦ እንዲፈርም የተገለጸበት ደብዳቤ፣
  - ✓ ከመስሪያ ቤቱ ጋር የተፈራረመውን ውል፣
  - ✓ ከመስሪያ ቤቱ የተሰጠውን የግዢ ትዕዛዝ (Purchase Order)፣
  - ✓ ከመስሪያ ቤቱ የተሰጠውን የንብረት ማንሳት ትዕዛዝ፣
  - ✓ ከመስሪያ ቤቱ ጋር ግዢውን/ንብረት ሽያጩን በተመለከተ በየጊዜው የተለዋወጡት ደብዳቤና መረጃዎች፣
  - ✓ ስለቀረበበት የጥፋተኝነት ሪፖርት ምላሽ ወይም መግለጫ ከማስረጃ ጋር

3. **አቤቱታ ወይም የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚጣራበትና የውሳኔ አስተያየት የሚቀርብበት ቅደም ተከተል**

- የቀረበውን አቤቱታ ወይም የጥፋተኝነት ሪፖርት ከተሰጠው ምላሽና ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ አኳያ በጥልቀት በመመርመር ተጨማሪ ማስረጃዎች የሚያስፈልጉ ከሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ በማድረግና በማጣራት በጋራ ውይይት ተደርጉበት ከተጫራች የቀረበ አቤቱታ ከሆነ ለውሳኔ ሰጭ አካላት የውሳኔ አስተያየት አቅርቦ ማስወሰን፣ ከመንግስት መስሪያ ቤት በተጫራች ወይም በአቅራቢ ላይ የቀረበ የጥፋተኝነት ሪፖርት ከሆነ እንደ ጉዳዩ ክብደት እና ቅለት እየታየ በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤት አካላት ውሳኔ እንዲሰጥ ይደረጋል፣
- አቤቱታው የቀረበው ከጠቅሚ ወይም ከስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ከሆነ በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ ይደረጋል፣
- የመ/ቤቱ ኃላፊ ወይም የስራ ሂደቱ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ይፈረምበትና ለአቤቱታ አቅራቢው፣ ለግዢ ፈጻሚው አካል ወይም ለስነምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ወይም ተጫራች ወይም አቅራቢ በመንግስት ግዥ ወይም ንብረት ሽያጭ

ላይ እንዳይካፈል የማገድ ውሳኔ ከሆነ ለሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለፌዴራል የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለሌሎች ክልልሎች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች በጽሁፍ ይተላለፋል።

4. የሚሰጥ ውሳኔ

ውሳኔ ሰጭው አካል / በየደረጃው ያለ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤት / በተጨራች ወይም በአቅራቢው ወይም በንብረት ገዢ ላይ የሚሰጠው ውስኔ፣

ውሳኔ ሰጭው አካል፡- ጥፋተኛ ሆኖ ባገኘው ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም ንብረት ገዢ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፣

- ✓ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ወይም፣
- ✓ በማንኛውም የመንግስት ግዢ/ንብረት ሽያጭ ጨረታ እንዳይሳተፍ ለተወሰነ ጊዜ ለመከልከል ከአቅራቢዎች ዝርዝር መሰረዝ ወይም፣
- ✓ ተጫራቹ ወይም አቅራቢው ወይም ንብረት ገዥው ጥፋተኛ ያለመሆኑን መግለጽ፣

የሚሰጠው ውሳኔ ማስጠንቀቂያ ከሆነ ውሳኔው ለራሱ ለተጫራቹ ወይም ለአቅራቢው ወይም ለንብረት ገዢው እና የጥፋተኝነት ሪፖርት ላቀረበው መስሪያ ቤት የሚተላለፍ ይሆናል።

የሚሰጠው ውሳኔ ተጫራቹን ወይም አቅራቢውን በመንግስት ግዥ ወይም ሽያጭ ጨረታ ውስጥ እንዳይሳተፍ ማገድ ከሆነ ውሳኔው ለሚከተሉት አካላት ይተላለፋል፣

- ✓ ለተጫራቹ ወይም ለአቅራቢው ወይም ለንብረት ገዢው ለራሱ ፣
- ✓ የጥፋተኝነት ሪፖርት ላቀረበው መስሪያ ቤት፣
- ✓ በክልል ለሚገኙ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች፣
- ✓ ለሁሉም ክልሎችና ለአዲስ አበባና ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች፣ ለፌዴራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

በየደረጃው የሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት በመስሪያ ቤቶች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ከሆነ፣ በመስሪያ ቤቱ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፣

- መስሪያ ቤቱ ህጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን ውሳኔውን እንዳይሰጥ ማገድ፣
- መስሪያ ቤቱ ከህግ ውጭ የሆነውን የግዢ ስርዓት እንዳይከተል ማድረግ ወይም በግዢና ንብረት አዋጁ በተደነገገው መሰረት ስራውን እንዲያከናውን ውሳኔ ማስተላለፍ፣
- መስሪያ ቤቱ ከህግ ውጭ ያከናወነውን ተግባር ወይም የሰጠውን ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ማድረግ፣
- ጨረታውን መሰረዝ፣

- መስሪያ ቤቱን ጥፋተኛ ሆኖ ካላገኘው አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ ፣

በአጠቃላይ በቀረበው ቅሬታ ላይ ማስረጃ፣ መግለጫና ሰነዶች ለመጠየቅ፣ ጉዳዩን ለማጣራትና ውሳኔውን በዕሁፍ ለማስተላለፍ አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በሚቆጠር አስቢ የስራ ቀናት ውስጥ ለውሳኔው መሰረት የሆኑትን ምክንያቶችና የተወሰዱትን የመፍትሄ እርምጃዎች በመጥቀስ ውሳኔ ይተላልፋል::

5. በመስሪያ ቤት ወይም በተጫራች ወይም በአቅራቢ ወይም በንብረት ገዢ ላይ የሚተላለፍ የውሳኔ ደብዳቤ ሊይዛቸው የሚገቡ ነጥቦች እና ከውሳኔው ጋር በአባሪነት የሚያያዙ ማስረጃዎች፣

- ✓ የውሳኔው ደብዳቤ ወጪ የሚደረግለትን አካል ስምና አድራሻ (ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም ንብረት ገዢ ከሆነ ስልክ ቁጥር፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥርን) ይይዛል
- ✓ የቀረበው አቤቱታ ወይም የጥፋተኝነት ሪፖርት ርዕስ /ጉዳዩ፣... /
- ✓ የቀረበው አቤቱታ ወይም የጥፋተኝነት ሪፖርት ይዘት በአጭሩ፣
- ✓ አቤቱታው ወይም የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በየደረጃው የሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላትየቀረበበት፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት መግለጫና ማስረጃ እንዲቀርብ የጠየቀበት እና ምላሽ የተሰጠበት ደብዳቤዎች ቁጥርና ቀን፣
- ✓ ተጫራቹ ወይም ንብረት ገዢው ያቀረበው አቤቱታ ፍሬ ሃሳብ ጭብጥ እና መስሪያ ቤቱ የሰጠው መግለጫ ወይም ምላሽ ጭብጥ/ መስሪያ ቤቱ ያቀረበው የጥፋተኝነት ሪፖርት ፍሬ ሃሳብ ጭብጥ እና ተጫረቹ አቅራቢው ወይም ንብረት ገዢው የሰጠው መግለጫ ወይም ምላሽ ጭብጥ ፣
- ✓ በውሳኔ ሰጭ አካላት/በየደረጃው ከገንዘበብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት የተሰጠ ውሳኔ
- ✓ ግልባጭ የሚደረግላቸው አካላት ስምና አድራሻ፣
- ✓ ከግዢው ወይም ከንብረት ሽያጩ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችና ሰነዶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

6. ተጫራቾች ወይም ንብረት ገዢዎች የግዥ/የንብረት ማስወገድ አፈፃፀም አቤቱታ ወይም መስሪያ ቤቶች የጥፋተኝነት ሪፖርት ሲያቀርቡ ሊያሟሉ የሚገባቸው መረጃና የአቀራረብ ስርዓት

ተጫራቾች ወይም ንብረት ገዢዎች፣

ተጫራቾች/ንብረት ገዢዎች በመጀመሪያ አቤቱታቸውን ለባለበጀት መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ላቀረቡት አቤቱታ የተሰጣቸው መልስ ያላረካቸው ከሆነ ወይም አቤቱታውን

ባቀረቡ የግዥ አዋጁና መመሪያ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ባለበጀት መስሪያ ቤቱ ምላሽ ካልሰጣቸው አቤቱታ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት ማቅረብ ይችላሉ:: ውሳኔ በተሰጣቸው በ5 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ሲያቀርቡ እንደ ግዢው ዓይነትና እንደ አቤቱታው ክብደት መጠን የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፣

- የደረሰባቸውን በደል ወይም ጉዳት በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ የሚያብራራ የመስሪያ ቤቱን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና የግዢውን/የሽያጩን ዓይነትና ዘዴ የያዘ መግለጫ፣
- የራሳቸውን አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣
- ለመስሪያ ቤቱ ያቀረቡትን የአቤቱታ ደብዳቤ እና መልስ ተሰጥቷቸው ከሆነ የተሰጠውን መልስ ኮፒ፣
- አቤቱታውን በትክክል ይገልጻሉ የተባሉ ማናቸውም ከግዢው/ከሽያጩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና ከመስሪያ ቤቱ ጋር የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች፣
- ለተጠቀሰው ጨረታ የተሸጠላቸውን ወይም የተሰጣቸውን የጨረታ ሰነድ፣
- ለመስሪያ ቤቱ ያቀረቡትን የመጫረቻ /የመወዳደሪያ/ ሰነድ፣
- ከመስሪያ ቤቱ የተጻፈ የአሸናፊነት መግለጫ ደብዳቤ፣
- መስሪያ ቤቱ የሰጣቸውን የግዢ ትዕዛዝ (Purchase Order) /የንብረት ማንሳት ትዕዛዝ፣
- ከመስሪያ ቤቱ ጋር የተፈረመ የውል ሰነድ ፣
- ፕሮፎርማ ግዢ ከሆነ ለመስሪያ ቤቱ የቀረበ የፕሮፎርማ ቅጽ ኮፒ፣
- ውል እንዲፈርሙ የተገለጸበትን ደብዳቤ ፣

የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣

መስሪያ ቤቶች በአቅራቢው/በንብረት ገዢ ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት በየደረጃው ላሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ሲያቀርቡ ለጥፋቱ መነሻ የሆነውን ነገር የጥፋተኝነት ሪፖርት ማድረጊያ ፎርምን በመጠቀም ማቅረብ አለባቸው:: /ፎርሙ/ /በአባሪነት ተያይዟል/:: የጥፋተኝነት ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርሙ የሚከተሉትን ነጥቦች በዋናነት የሚጠይቅ ነው::

ሀ/ <u>ለግዥ</u>፣

- የባለበጀት መስሪያ ቤቱን ሙሉ ስም፣
- የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም ግንባታ ስራ ዓይነትና መጠሪያ፣
- ግዢው የተፈጸመበት የግዢ ዘዴ፣

- ጥፋቱን ፈጸመ የተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ስም፣ አድራሻ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር፣ ፋክስ ቁጥር
- የጥፋቱ ዋና ዋና ጭብጦች፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ውል የገባበትን ግዴታ እንዲወጣ በመስሪያ ቤቱ የተደረገ ጥረት፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ዕቃውን ባለማቅረቡ ወይም አገልግሎቱን ባለመስጠቱ ወይም ግንባታውን ባለማከናወኑ የሰጠው ምክንያት፣
- ጥፋት ፈጸመ በተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ በመስሪያ ቤቱ የተወሰደ እርምጃ፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ዕቃውን ባለማቅረቡ ወይም አገልግሎቱን ባለመስጠቱ ወይም ግንባታውን ባለማከናወኑ በመስሪያ ቤቱ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ኪሳራ፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ተጫራች ወይም አቅራቢ ዕቃውን ባለማቅረቡ ወይም አገልገሎቱን ባለመስጠቱ ግዢውን ለመፈፀጸም በመስሪያ ቤቱ የተወሰደ አማራጭ እርምጃ፣
- የተጫራቹን ወይም የአቅራቢውን ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ በየደረጃው ለሚገኙ የግንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት በማስረጃነት የቀረቡ ሰነዶች፣
- አሁን የጥፋተኛነት ሪፖርት የቀረበበት ተጫራች ወይም አቅራቢ ቀደም ሲል በመስሪያ ቤቱ የግዥ ወይም የሽያጭ አፈጻጸም ላይ ያሳየው የአፈጻጸም ሁኔታ /ጠንካራ ወይም ደካማ አፈጻጸም/

ለ/ ለንብረት ሽያጭ

- የመስሪያ ቤቱን ሙሉ ስም፣
- የሚሸጠው ዕቃ ዓይነትና መጠሪያ
- ሽያጩ የተፈጸመበት ዘዴ /ሃራጅ ወይም ጨረታ/፣
- ጥፋቱን ፈጸመ የተባለው ንብረት ገዢ ስም አድራሻ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣
- የጥፋቱ ዋና ዋና ጭብጦች፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ንብረት ገዢ ውል የገባበትን ግዴታ እንዲወጣ በመስሪያ ቤቱ የተደረገ ጥረት፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ንብረት ገዢ ዕቃውን ላለማንሳቱ የሰጠው ምክንያት፣
- መስሪያ ቤቱ ጥፋት ፈጸመ በተባለው ንብረት ገዢ ላይ የወሰደው እርምጃ፣
- ጥፋት ፈጸመ የተባለው ንብረት ገዢ ግዴታውን ባለመወጣቱ በመስሪያ ቤቱ የተወሰደ አማራጭ እርምጃ፣
- የንብረት ገዢውን ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ በየደረጃው ለሚገኙ የግንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አካላት በማስረጃነት የቀረቡ ሰነዶች፣

አባሪ 1

ጥፋት በፈጸመ የአገር ውስጥ ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም ንብረት ገዢ ላይ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ሪፖርት ማድረጊያ ፎርም

1. የመስሪያ ቤቱ ስም ----------
2. የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ/የሚሸጠው ንብረት ዓይነት ----------
3. ግዥው /ሽያጩ የተፈጸመበት የግዥ/ የሽያጭ ዘዴ ----------
4. ጥፋቱን የፈጸመው ተጫራች/አቅራቢ ስም.....
   .....ክፍለ ከተማ ..... ቀበሌ..... የቤት ቁጥር.....
   ፖ.ሳ.ቁ. ..... ስልክ ቁ ..... / ..... ፋክስ ቁ .....
5. እንደ አስፈላጊነቱ ጥፋቱን የፈጸመው አቅራቢ የአቅራቢነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቁጥር ----------
   ----
6. የጥፋቱ ዓይነት ----------
7. የአቅራቢውን ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ በማስረጃነት የቀረቡ ሰነዶች፡
   1 ----------
8. ጥፋት ፈጻሚው አቅራቢ ውል እንዲፈርም ወይም ውል የገባበትን ግዴታ እንዲወጣ በመስሪያ ቤቱ የተደረገ ጥረት
   1. ----------
   2. ----------
9. ጥፋት ፈጻሚው ተጫራች ወይም አቅራቢ ውል ላለመፈረም ወይም ዕቃውን ላለማቅረቡ ወይም አገልግሎቱን ላለመስጠቱ ወይም ግንባታውን ላለማከናወን ወይም የገዛውን እቃ ላለማንሳቱ የሰጠው ምክንያት.....
10. በጥፋት ፈጻሚው ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ በመስሪያ ቤቱ የተወሰደ እርምጃ
    1 ----------
11. ጥፋት ፈጻሚው ተጫራች ወይም አቅራቢ ውል ባለመፈረሙ ወይም ዕቃውን ባለማቅረቡ ወይም አገልግሎቱን ባለመስጠቱ ወይም ግንባታውን ባለማከናወኑ
    በመስሪያ ቤቱ ተግባር ላይ የደረሰ ጉዳት ወይ ኪሳራ ----------
    ----
12. ጥፋት ፈጻሚው ተጫራች ወይም አቅራቢ ዕቃውን ባለማቅረቡ ወይም አገልግሎቱን ባለመስጠቱ ወይም ግንባታውን ባለመፈጸሙ ግዢውን ለመፈጸም በመስሪያ ቤቱ የተወሰደ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ
    ----
13. አሁን የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት አቅራቢ ቀደም ሲል በመ/ቤቱ ግዢ አፈጻጸም ላይ ያሳየው የአፈጻጸም ሁኔታ /ጠንካራ ወይም ደካማ/ ካለ ይገለጽ ----------

ፎርሙን የሞላው አካል ስምና ፊርማ ቢቀመጥ_____

Public Procurement and prop/Admi/Cor Process

Complaints Submission Form /International Procurement/

1. Name of the Public Body.....
2. Type of Goods or Services or works Procured .....
   .....
3. Method of Procurement Performed.....
4. Name of the Offending bidder or supplier ..... Tel.
   ...../..... Fax no. ..... Address
   ..... P.O.Box ..... E-Mail .....
5. Name of the Local Agent for the Foreign Offending Supplier..... Sub
   City..... Kebele ..... House No. ..... Tel.
   ...../..... Fax no..... P.O.Box .....
6. Type of the Offence Committed by the bidder or Supplier.....
   .....
7. Documents Attached to Confirm the Offence of the Supplier:
   1. .....
   2. .....
8. Efforts made by the Procuring Entity to make the Offending Supplier fulfilling its Obligations.
   1. .....
   2. .....
9. Reasons given by the Supplier why the bidder or supplier failed to perform Accor-
   ding to the Contract.....
10. Measures taken on the Offending bidder or supplier by the publib body:
    1. .....
11. Injury or loss faced by the Procuring Entity due to failure of the Offending Supplier to fulfil its
    Obligations ....
12. Alternative measure taken by the Procuring Entity to Procure the Goods or Services
    .....
13. Explain Situation of Previous Performances /good or bad/ of the Offending Supplier
    .....